# ሆ,ያ ሆዬ

ሆያ ሆዬ! ሆ!...ሆያ ሆዬ! ሆ!

መጣና ጌታችን
እንደልምዳችን ።
  ክፈት በለው ፤ በሩን
  የምርጫውን ።

ሆያ ሆዬ! ሆ!...ሆያ ሆዬ! ሆ!

እዚያ ማዶ ፤ ወንበር አለ
ያስቀምጣል ፤ ላልታገለ
ከፓርላማው ፤ አስቀምጡን
እናጨብጭብ ፤ ወንበር ስጡን
በትግል ሰበብ ፤ እንግባ ፤ መሃል
ካመረርንማ ፤ ይጨርሱናል
አጎንባሽ ፤ ቢሉህ ፤ አትስጠው ፤ ጆሮ
ጠላት ፤ ኃያል ነው ፤ ማን ይንካ ፤ ደፍሮ ።

ሆይሽይ ፤ ሎሚታ
እስቲ ፤ እናምታታ ።
  ሆይሽይ ፤ ሎሚታ
  እስቲ ፤ እናምታታ ።

አጋፋሪ ፤ ሕብረት ፤ ፈጥሯል
ባክራሪዎች ፤ ተወጥሯል
እጅ ፤ እንዳንሰጥ ፤ ችግር ፤ ፈጥሯል
ያገለግላል ፤ ፈሪ ለጌታው
ለመኖር ሲባል ፤ መመሳሰል ነው
ለድል ላንበቃ ፤ ከንቱ ድካም ነው
ደከመን ፤ በቃ ፤ ብዙ ፤ ተለፋ
አትነካኩን ፤ ቆጠናል ፤ ተስፋ ።

መጣና ጌታችን
እንደልምዳችን ።
  ክፈት በለው ፤ በሩን
  የምርጫውን
ክፈት በለው ፤ በሩን
ፓርላማውን ።